https://chilot.me


የኢትዮጵያፌደራላዊዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ

# ፌደራልነጋሪትጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፹፩
አዲስ አበባ ነሀሴ ፳፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23th Year No.81
ADDIS ABABA 29th August, 2017


**ማውጫ**

**CONTENTS**


ደንብ ቁጥር ፬፻፱/፪ሺ፱ ዓ.ም

የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………………………………...ገጽ፱ሺ፰፻፵፪

Regulation No. 409/2017

Ethiopian Foreign Relations Services Training Institute Establishment Council of Ministers Regulation ………………………………………………..Page 9842


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፱/፪ሺ፱

## የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፱ እንዲሁም በውጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፯፻፺/፪ሺ፭ አንቀጽ ፶(፪) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፱/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪.ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "አዋጅ" ማለት የውጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፯፻፺/፪ሺ፭ ነው፤

፪/ በአዋጁ የተሰጠ ትርጓሜ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 409/2017

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN FOREIGN RELATION SERVICES TRAINING INSTITUTE

This Regulation is issued by the Council of Minister pursuant to Article 5 and 39 of the definition of powers and duties of the executive organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation NO. 916/2015 and Article 50(2) of the Foreign Services proclamation NO. 790/2013.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Foreign Relations Services Training Institute Establishment Council of Ministers Regulation NO. 409/2017".

**2. Definition**

In this Regulation:

1/ "proclamation" mean the Foreign Services Proclamation NO. 790/2013;

2/ the definitions provided under the proclamation shall also apply.

**፫. መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ተቋም (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩቱ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

**፬. ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

**፭. ዓላማ**

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ፡-

፩/ በውጭ ግንኙነት አገልግሎት የሙያ ብቃት እና ክህሎት ያለው፣ በአህጉራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ በላቀ ሁኔታ ተወዳዳሪ የሆነ፣ በየደረጃው የተቀመጠውን የሙያ ክህሎት ያሟላ፣ አገራዊ ተልዕኮውን በብቃት መወጣት የሚችል የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ ማፍራት፣ እና

፪/ የሚኒስቴሩን የዲፕሎማሲያዊ አቅም በማጠናከር አገራችን በውጭ ግንኙነት ያላትን ተደማጭነት በአህጉራዊና ዓለም አቀፍ ደረጃ ማጎልበት፣ ይሆናል።

**፮. የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞችን የዲፕሎማሲ ሙያ ክህሎት ለማዳበር የሚያስችል ሥርዓተ-ትምህርት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር ማዘጋጀት፤

፪/ የሥልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፣ ለአዳዲስ ዲፕሎማቶች የዲፕሎማሲ ክህሎት ሥልጠና መስጠት፤

፫/ ስልጠናቸውን በአጥጋቢ ውጤት ላጠናቀቁ አዳዲስ ዲፕሎማቶች ድህረ-ምረቃ ዲፕሎማ ይሰጣል።

፬/ ትምህርታዊ ውይይት፣ ሴሚናሮች እና ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ማከናወን፤

፭/ ከአንድ የሥራ ደረጃ ወደ ሌላ የሥራ ደረጃ ለሚያድጉ ሠራተኞች የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፤

፮/ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች በያዙት ደረጃ የሥራ አፈፃፀማቸውን ለማዳበር የሚረዳ ተጨማሪ የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠት፤

**3. Establishment**

1/ The Ethiopian Foreign Relation Services Training Institute (in this regulation referred to as "the institute") is hereby established as an autonomous Federal Government Institute having its own legal personality.

2/ The institute shall be accountable to the Ministry.

**4. Head Office**

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

**5. Objectives**

The objectives of the institute are to:

1/ produce professionally qualified and skilled foreign relation service officers that demonstrate high level competence at regional and international stages, who fulfills the professional requirements set at different levels and capable to execute the missions of the nation; and

2/ strengthen the diplomatic capability of the ministry and thereby contribute to the audibility of the country at international and regional stages.

**6. Powers and Responsibilities of the Institute**

The institute shall have the following powers and duties:

1/ prepare, in cooperation with other appropriate organs, a curriculum that aims at improving the diplomacy skill of foreign relations service officers;

2/ prepare training manuals and train new diplomatic service recruits;

3/ issue a post-graduate diploma to new diplomatic service recruits who completed the training with satisfactory results.

4/ organize seminars and workshops, and conduct other related activities;

5/ provide foreign relations service trainings foreign relation service officers who are going to be promoted to the next career ladder;

6/ provide additional capacity building training on the current positions by for foreign relations service officers;

https://chilot.me


፯/ ዝቅተኛ የሥራ አፈጻጸም በማግኘታቸው ምክንያት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ቋሚ ሠራተኞች ሥልጠና መስጠት፣

፰/ የውጭ አገር ቋንቋ ክህሎት ማሻሻያ ሥልጠናዎችን መስጠት፣

፱/ የሚኒስቴሩ የፈተናዎች አስተዳደር ቦርድ ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞችን ሙያዊ ብቃት፣ የውጭ ቋንቋ እና የመረጃ ቴክኖሎጂ ዕውቀት ለማረጋገጥ የሚያስችል መደበኛ የሆነ የብቃት ማረጋገጫ ፈተና ማዘጋጀት፣ መፈተን፣ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት፣

፲/ የመስሪያ ቤቱን የሰው ሀይል ልማት መሰረት ያደረገ የሥልጠና ፍላጎቶች በጥናት መለየት፣

፲፩/ በዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት እውቀትና ልምድ ያላቸው ምሁራን፣ ጡረታ የወጡ ወይም በሥራ ላይ ያሉ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች መካከል ለማሰልጠን ብቃት ያላቸውን በመለየት ሥልጠና የሚሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

፲፪/ ሚኒስቴሩን በማስፈቀድ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ሌሎች ዓለም አቀፍና ሀገር-በቀል ተቋማት ጋር የልምድና የሰው ኃይል ልውውጥ ማድረግ፣ ግንኙነቶችን መመስረትና በጋራ ሥልጠናዎችን መስጠት፣

፲፫/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በስሙ መክሰስና መከሰስ፣

፲፬/ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ማናወን።

## ፯. <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ፡-

፩/ አማካሪ ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ)፣

፪/ በመንግሥት የሚሰየሙ ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ እና

፫/ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## ፰. <u>የቦርዱ የአባላት</u>

፩/ ቦርዱ ሰብሳቢውን እና ምክትል ሰብሳቢውን ጨምሮ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግስት የሚሰየሙ እና ቁጥራቸው እንደ አስፈላጊነቱ የሚወሰኑ አባላት ይኖሩታል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሰየሙ የቦርዱ አባላት ያላቸው የትምህርት ዝግጅት፣ ዕውቀት፣ ለኢንስቲትዩቱ ተግባርና

7/ provide training to underperforming permanent foreign relation service officers;

8/ provide foreign language proficiency trainings;

9/ without prejudice to the powers and responsibilities of the Ministry’s Examinations Administration Board, prepare and regularly administer examinations and issue certificates on the professional skills, foreign language, and information technology knowledge of foreign relation service officers;

10/ identify the training needs for the human resource development of the ministry;

11/ facilitate the provision of training by scholars who have knowledge and experience on diplomacy and international relations, retired or current foreign service officers who are capable of providing training;

12/ with the permission of the ministry, share experience, create partnerships, engage in exchange programs and conduct training in cooperation with both domestic and international institutions having similar objectives;

13/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

14/ undertake other activities necessary for the attainment of its objectives.

## 7. <u>Organization of the Institute</u>

The institute shall have:

1/ an advisory board (in this regulations referred to as the “board”);

2/ a director general and deputy director general to be assigned by the government; and

3/ the necessary staffs.

## 8. <u>Members of the Board</u>

1/ The members of the board including the chairperson and deputy chairperson shall be assigned by the government up on nomination by minister and their numbers shall be determined as may be necessary.

2/ The assignment of members of the board pursuant to sub-article (1) of this article shall be made based on their academic background, knowledge, their relevance for the accomplishment of the

https://chilot.me


ዓላማዎች ያላቸው አግባብነት እና ለአገራችን የውጭ ግንኙነት መሻሻል ሊያበረክቱት የሚችሉትን አስተዋጽኦ መሠረት ያደረገ ይሆናል።

፫/ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ይሆናል።

## ፱. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ኢንስቲትዩቱ በሚሰጣቸው ሥልጠናዎች ላይ ኢንስቲትዩቱን ያማክራል፤

፪/ ኢንስቲትዩቱ የሚያከናውናቸውን ሥራዎች በማቀድና የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በማድረግ ረገድ ምክር ይሰጣል፤

፫/ ከዋና ዳይሬክተር በሚቀርቡለት ሌሎች ጉዳዮች ላይ በመምከር የውሳኔ ሀሳቦችን ያቀርባል።

## ፲. የቦርዱ ስብሰባዎች

፩/ ቦርዱ መደበኛ ስብሰባውን በየሦስት ወሩ እና አስቸኳይ ስብሰባዎችን እንደአስፈላጊነቱ ያደርጋል፡፡

፪/ ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ የቦርዱ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፩. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣን እና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት ኢንስቲትዩቱን ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኢንስቲትዩቱን ሰራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ህጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

objectives and responsibilities of the institute, and their contribution to the betterment of Ethiopia's foreign relations.

3/ The director general of the institute shall be a member and secretary of the board.

## 9. Powers and Duties of the Board

The board shall have the powers and duties to:

1/ advise the institute on the training it provides;

2/ advise the institute in relation with the preparation and evaluation of its plan of activities;

3/ consult and provide recommendations on other matters presented to it by the director general.

## 10. Meetings of the Board

1/ The board shall hold its ordinary meetings every three months and may hold extraordinary meetings as may be necessary.

2/ There shall be quorum where more than half of the members of the board are present at a meeting.

3/ The decisions of the board shall be made by a majority vote and, in the case of a tie, the chairperson shall have a casting vote;

4/ without prejudice to the provisions of this article, the board may adopt its own rules of procedure.

## 11. Powers and Duties of the Director General

1/ The director general shall be the chief executive officer of the institute and shall, subject to the general directions of the ministry, direct and administer the activities of the institute.

2/ without prejudice to the generality sub-article (1) of this article, the director general shall:

a) exercise the powers and duties of the institute specified under article 6 of this regulation;

b) employ, administer and fire employees of the institute in accordance with the federal civil service laws;

https://chilot.me


ሐ) የኢንስቲትዩቱን ዕቅድ አዘጋጅቶ ከቦርዱ አስተያየት ጋር ለሚኒስቴሩ ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ከቦርዱ አስተያየት ጋር ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ በመንግሥት ሲጸድቅ ሥራ ላይ ያውላል፤

ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች በማዘጋጀት ከቦርዱ አስተያየት ጋር ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተርና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፲፪. <u>በጀት</u>**

የኢንስቲትዩቱ በጀት ከመንግስት የሚመደብ ይሆናል፡፡

**፲፫. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉ እና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይኖሩታል፤

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

**፲፬. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፭. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፫ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

c) prepare and present the institute's work plan to the ministry by including the board's comment and implement same upon approval;

d) prepare and present the institute's annual budget to the ministry including the board's comment and implement the same upon approval by the government;

e) represent the institute on its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the ministry the performance reports of the institute together with the board's recommendation;

3/ The director general may delegate part of his powers and duties to the deputy director general and other employees of the institute to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the institute.

**12. <u>Budget</u>**

The budget of the institute shall be allocated by the government.

**13. <u>Books of Accounts</u>**

1/ The institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the institute shall be audited annually by the auditor general or by an auditor assigned by him.

**14. <u>Power to Issue Directive</u>**

The ministry may issue directives necessary for the implementation of this regulation.

**15. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter in to force on the date of Publication on the Federal Negarit gazette.

**Done at Addis Ababa, this 29th day of August, 2017.**

**HAILEMARIAM DESSALEGNE**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATICREPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://chilot.me